የሠ/መ/ቁ. 20325

29-06-98

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አቶ ጌታቸው ምህረቱ

ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ታምራት መሸሻ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ፊጣ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02272 በ28/8/96 ዓ.ም. የሠጠውን ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሠበር ችሎት በመ.ቁ. 13459 በ18.8.97 እና በመ.ቁ. 27422 በ24.9.97 በማፅናታቸው ነው።

ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ክርክር የአሁን መልስ ሰጪ በአፈፃፀም ክስ በአሁን አመልካች ላይ በዋናው ውሣኔ ላይ እንዲከፍል የተወሠነውን ብር 5050.00/አምስት ሺ አምሳ ብር/ እንዲከፍል ከጠየቀ በኂላ አፈፃፀሙን በማቋረጥ 10 ዓመት ካለፈ በኂላ መዝገቡን በማንቀሳቀስ አፈፃፀሙን ቢቀጥልም ጉዳዩ የቀረበለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ክሱ መቅረብ ያለበትን የይርጋ ጊዜ በተመለከተ ያስረዳው ነገር የለም በማለት ወስኖአል። ጉዳዩን በይግባኝ ያዩትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሠበር ችሎት ይግባኙን ሳይቀበሉት ቀርተዋል። የአሁን

ፊርማ ___ ቀን 14/7/98

አመልካች የሠበር አቤቱታ ዋነኛ የቅሬታ ነጥብም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 384/ሀ/ መሠረት የአፈፃፀም ክሱ ከተቋረጠ በኋላ 10 ዓመት ከ3ወር በኋላ በመቅረቡ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑና አመልካችም ልጠየቅ እንደማይገባኝ እያመለከትኩ ፍ/ቤቱ አፈፃፀሙን ቀጥሎ እንዲታይ የሠጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ትዕዛዝ ያለው በመሆኑ እንዲሻር በማለት ነው፡፡

የሠበር ችሎቱ ጉዳዩ በሠበር እንዲታይ በመወሠኑ መልስ ሰጪ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን የቃል ክርክር እንዲያሠሙ ተደርጓል፡፡ የክርክራቸው መሠረታዊ ይዘትም የአሁን አመልካቾች በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ብለው ስንከራከር በመቆየታችን አፈፃፀሙን ያቋረጥኩት ይግባኙ ካለቀ በኋላ እንደገና አንቀሳቀስኩ ይሄ ደግሞ አስር ዓመቱን አያሳልፍም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በክርክራቸው አቋማቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በሥነ ሥርዓት ሕጎች ላይ የተደነገጉትን የጊዜ ገደቦችን ፍ/ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ተፈፃሚነታቸው ሊከታተሉ ይገባል ወይንስ እንደ ሥረ ነገር የይርጋ ህጎች በተከራካሪ ወገን ካልተነሡ እንደተተወ ይቆጠራል የሚሉትን የሕግ ነጥቦች የሚያስነሳ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ይህንኑ ነጥብ መርምሯል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ ለመረዳት እንደቻልነው ፍ/ቤቱ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያዘዘው የአሁን አመልካች ክሱ መቅረብ ያለበትን የይርጋ ጊዜ በመለከተ ክርክሩን በቃል በሚያሰረዳበት ጊዜ ያስረዳው አንዳችም ነገር የለም በማለት ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 384 መሠረት " አንድ የተለየ ነገር እንዳይፈፀም ፍርድ ቤቱ ከሚሠጠው የማገጃ ትዕዛዝ በቀር ፍርድ እንዲፈፀም ማመልከቻ ቀርቦ ዓስር ዓመት ከቆየና ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ሌላ ማመልከቻ በማቅረብ ነገሩን ለማንቀሳቀስና ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ አይቻልም" በማለት ይደነግጋል፡፡



ፊርማ 1ኛ 14/7/98

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ የሙግትን ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ የተለያዩ የጊዜ ገደቦችን ያስቀመጠ መሆኑን፣ አላማቸውም በሙግት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በሕጉ በተቀመጠው አሊያም ፍ/ቤቱ በሚወሰነው የጊዜ የገደብ ውስጥ መከናውን ያለበት መሆኑን፣ ካልሆነ ሕጋዊ ውጤት እንደሌላቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አላማ ደግሞ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሠ ወጪ በተቀላጠፈ እና ፍትሐዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያኙ ማድረግ በመሆኑ የተዋዋዮችን ጥቅም ለመጠበቅ ከተደነገገው የዋናው ሕግ አላማ የተለየ እና ፍርድ ቤቶችም በሥነ ሥርዓት ሕጉ በግልፅ የሠፈረ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሚቀርብን ክስ በራሳቸው አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ ትክክለኛ አካሄድ ለመሆኑ ይህ የሠበር ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 17361 ሐምሌ 25 ቀን 1997 ዓ.ም. በሠጠው ውሣኔ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

በዚህ መዝገብ ከቀረበው ጉዳይ ለመረዳት እንደቻልነው የአሁን ተጠሪ ታህሣስ 14 ቀን 1986 ዓ.ም. ውሣኔ የተወሠነለት ሲሆን በውሣኔውም መሠረት የአፈፃፀም ክሱን በ30/7/96 ዓ.ም. ካቀረበ በኋላ አፈፃፀሙን በማቋረጥ እንደገና በመጋቢት 30 ቀን 1996 ዓ/ም የሥር ፍ/ቤትን የአፈፃፀሙን መዝገብ አንቀሳቅሷል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ተጠሪው የአፈፃፀሙን መዝገብ ካቋረጠ በኋላ 10 ዓመት ከ3ወር በኋላ ማንቀሳቀሱን ነው፡፡ ይህም የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 384 /ሀ/ ያስቀመጠውን የ10 ዓመት የጊዜ ገደቡን ማለፉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ገደብ ያልጠበቀ ነገር በሚቀርብለት ጊዜ ደግሞ ፍ/ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን ተቃውሞ ሳይጠብቅ በራሱ ተነሳሽነት ውድቅ ማድረግ ሲኖርበት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ከፍተኛው ፍ/ቤት ተቃውሞውን ተጠሪው አንስቶ አልተከራከረም በማለት የሠጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የሠበር

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ____ ቀን 14/7/98

ችሎቱ ይህንን ስህተት ማረም ሲኖርባቸው ውሣኔውን ማፅናታቸው ስህተት በመሆኑ ውሣኔው ተሽሯል።

## ው ሣ ኔ

- የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሯል።
- ተጠሪ 10 ዓመት ካለፈ በኋላ የአፈፃፀሙን መዝገብ ለማንቀሳቀስ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ታግዷል።
- ግራ ቀኙ ወጪአቸውን ይቻቻሉ።

የማይነበቡ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 14/7/98